የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፩
አዲስ አበባ ህዳር ፫ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No.1
ADDIS ABABA 12th November, 2014


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፰፻፷፯/፪ሺ፯ ዓ.ም

በዓለም አቀፍ የካፒታል ገበያ የሚሸጡ የመንግሥት ዕዳ ሰነዶች አዋጅ..........................ገጽ ፯ሺ፯፻፮


CONTENTS


Proclamation No. 867/2014

Government Bonds Transacted in International Capital Markets Proclamation..................Page7706


## አዋጅ ቁጥር ፰፻፷፯/፪ሺ፯

## በዓለም አቀፍ የካፒታል ገበያ ስለሚሸጡ የመንግሥት ዕዳ ሰነዶች የወጣ አዋጅ

ለመሠረተ ልማት ግንባታ የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሪ ወጪ ለመሸፈን የሚያግዝ ገንዘብ የመንግሥት ዕዳ ሰነዶችን በዓለም አቀፍ የካፒታል ገበያ በመሸጥ ማሰባሰብ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በዓለም አቀፍ የካፒታል ገበያ የሚሸጡ የመንግሥት ዕዳ ሰነዶች አዋጅ ቁጥር ፰፻፷፯/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION No. 867/2014

## A PROCLAMATION ON GOVERNMENT BONDS TO BE TRANSACTED IN INTERNATIONAL CAPITAL MARKETS

WHEREAS, it has become necessary to raise fund to finance the foreign currency requirements of infrastructure projects by issuing Government Bonds to be transacted in international capital markets;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as "Government Bonds Transacted in International Capital Markets Proclamation No.867/2014."

## ፪. የመበደር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ በዓለም አቀፍ የካፒታል ገበያ የሚሸጡ የመንግሥት የዕዳ ሰነዶችን በማውጣት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ስም እስከ ሁለት ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሚደርስ ብድር እንዲወስድ በዚህ አዋጅ ተፈቅዷል።

## ፫. ክፍያና ወለድ

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ የመንግሥት የዕዳ ሰነድ የሚወጣበትን ቀን ለመወሰን፣ ዕዳው ተከፋይ የሚሆንበትን ቀን እና የዕዳውን አከፋፈል እንዲሁም የወለዱን መጠን በሚመለከት ከአበዳሪዎች ጋር ለመስማማት ይችላል።

## ፬. ከቀረጥና ግብር ነፃ ስለመሆን

በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚወጡት የመንግሥት የዕዳ ሰነዶች ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ወይም ሰነዶች ላይ የቴምብር ቀረጥ ወይም ሌላ ማናቸውም ቀረጥና ግብር አይከፈልም።

## ፭. አዋጁ የሚፀናበት ቀን

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ህዳር ፫ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት



## 2. Authority to Borrow

The Minister of Finance and Economic Development is hereby authorized to borrow in principal amounts in the aggregate not exceeding two billion United States Dollars on behalf of the Federal Democratic Republic of Ethiopia by issuing Government Bonds to be transacted in international capital markets in one or more series.

## 3. Repayment and Interest

The Minister of Finance and Economic Development is authorized to determine the issuance date and agree with the lenders on the maturity dates, dates of repayment and rates of interest.

## 4. Exemption from Taxes and Duties

No stamp duty or any other tax may be levied on any transaction or document relating to the Government Bonds issued under this Proclamation.

## 5. Effective Date

This Proclamation shall enter into force and effect as of the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 12th day of November, 2014.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት